


http://www.hr2003.org // http://www.hr5680.org

*E-mail: passhr2003@hr2003.org*
*passhr5680@hr5680.org*

*Tel: 323-988-5688 Fax: 323-924-5563*

**FOR IMMEDIATE RELEASE**
**May 1, 2007**

# COALITION FOR H.R. 2003

**presents an**

# Amharic Translation of H.R. 2003

The Coalition for H.R. 5680 is pleased to present an Amharic translation of H.R. 2003 for its reading audience. The extraordinary translation work was done by Tekle Atalay, a human rights defender and Coalition supporter.

================================================================================

# ረቂቀ፡ ህግ፡ 2003

**(Translated by Tekle Atalay)**

# H.R. 2003

## በ110ኛው የዩናይትድ ስቴትስ ኮንግረስ የመጀመርያው ስብሰባ

### በኢትዮጵያ ሰላምንና ደህንነትን ለማዳበር፣ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ነፃነትን እንዲሰፍኑ ለማበረታታትና ለማመቻቸት

---

### በተወካዮች ምክርቤት የቀረበ

---

**ይህንን ህገ ያረቀቁት አቶ ፐይን (በራሳቸው ስምና ከዚህ ህገ-ረቂቅ ተያይዞ በተጠቀሱት ተባባሪ ህግ አርቃቂዎች) ሲሆኑ፤ ለሚከተለው ኮሚቴ ተላልፏል፡-**

### ሕገ-ረቂቅ

በኢትዮጵያ ሰላምንና ደህንነትን ለማዳበር፣ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ነፃነት እንዲሰፍን ለማበረታታትና ለማመቻቸት።

በተሰበሰበው የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ሴኔትና የተወካዮች ምክርቤት እንዲፀድቅ ይሁን።

ክፍል ፩. <u>የህገ-ረቂቁ አርዕስት</u>

ይህ ህገ-ረቂቅ "የ 2007 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ተጠያቂነት ድንጋጌ" በመባል ሊጠቀስ ይችላል።
ክፍል ፪. <u>የፖሊሲ አቋም</u>

የአሜሪካ መንግስት አቋም፦
1. በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች፣ የዴሞክራሲ፣ የፍርድቤቶች (ከሕግ-አውጪውና ስፈፃሚው) ተፅዕኖ ገለልተኝነት፣ የሕትመት (ፕሬስ) ነፃነት፣ የሰላምና የአቅም ግንባታ እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገት የሚጠበቁበትና የሚደገፉበት መንገደ ለመቀየስ፤

2. የፖለቲካና የሕሊና እስረኞችን ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ የሚፈቱበትን አማራጭ መሻት፤

3. በቀጠናው (በምሥራቅ አፍሪካ) መረጋጋትን፣ ዴሞክራሲንና የምጣኔ ሀብት እድገትን ማጎልበት፤

4. ፀረ-ዓለማቀፍ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት ከኢትዮጵያ ጋር ለመተባበር፤

5. ከቁጥር 1 እስከ 4 በተጠቀሱት ፖሊሲዎች መሟላትና ተግባር ላይ መዋል ተመስርቶ የአሜሪካና የኢትዮጵያ ግንኙነት ማጠናከር ናቸው።

ክፍል ፫. <u>ግንዛቤዎች</u>

ኮንግረስ የሚከተሉትን ይገነዘባል፦

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ በወታደራዊ ግጭቶች፣ በተፈጥሮ አደጋዎች፣ ድህነትና በሽታዎች፣ በአከባቢያዊ አለመረጋጋትና እንዲሁም በጨካኙ የመንግስቱ ኃ/ማርያም ውታደራዊ አገዛዝ ለአስርት ዓመታት ተሰቃይተዋል። ሴቶችንና ሕፃናትን ጨምሮ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኑፁሃን ዜጎች በጭካኔ ተገድለዋል። ሌሎች ብዙውችም ለነፃንት፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበርና የአምባገነኑን ስርዓት ለማስወገድ ሲሉ ሕይውታቸውን መስዋዕት ከፍለዋል። የዛ አምባገነን ስርዓት አባላት የነበሩት በአሁኑ ወቅት በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በአፍሪካ ይኖራሉ።

2. በግንቦት 1991 የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) አምባገነኑ መንግስቱ ኃ/ማርያምን ከስልጣን ካስወገደ በኋላ እንደ ኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) እና ሌሎች የነፃነት ግንባሮች እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመሆን የሽግግር መንግስት በሐምሌ 1991 አቋቁሟል።

3. መንግስቱ ኃ/ማርያም ከስልጣን ከተወገደ ከ1991 ወዲህ፤ በኢሕአዴግ የሚመራው መንግስት የምድብለ ፓርቲ ስርዓትን በማቋቋም ሶስት ክልላዊን ብሔራዊ ምርጫዎች እንዲሁም በርካታ አካባቢያዊ ምርጫዎችን አካሂዷል። በ1995 እና 2000 የተካሄዱ ምርጫዎች በአብዛኛው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያልተሳተፉበት የነበረ ሲሆን ምርጫዎቹም ነፃና ፍትሐዊ እንዳልነበሩ ይታወቃል። በ2000 ምርጫ የተወሰኑ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የተሳተፉ ሲሆን ከ546 የፓርሊያመንት መቀመጫዎች 12 አግኝተዋል።

4. የግንቦት 2005 ቅድመ-ምርጫና የምርጫው ክንውኖች ምንም እንኳን ችግሮች የነበሩበት ቢሆንም ግልጽነት፣ ከፍተኛ ፉክክር የታየበትና በአንፃሩ ነፃና ፍትሐዊ እንደነበር ታዛቢዎች ተመልክተዋል። ከተመዘገቡት መራጮች ከ90 በመቶ በላይ እንደተሳተፉበትና በደዘኖች የሚቆጠሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወዳድረዋል። በተጨማሪም አለማቀፍ ድርጅቶች መርጫውን የተከታተሉ ሲሆን፡ ተቃዋሚዎችም የመገናኛ ብዙሃን መጠቀም ችለው የነበረ ሲሆን መንግስትና ተቃዋሚዎች በቴሌቪዥን የላልፉ ክርክሮችን አድርገዋል። አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶችና የታጠቁ ሃይሎች በምርጫ 2005 ያልተሳተፉ ሲሆን የሰለጠኑ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ስራቸውን እንዳይሰሩ ታግደዋል።

5. ምንም እንኳን የምርጫ ሂደቱ መሻሻል ቢያሳይም፣ ምርጫ ቦርድ ቆጠራውን ሳያጠናቅቅ የኢትዮጵያ መንግስት አሸኒፌያለሁ ብሎ ማዋጁ ታዛቢዎችን አጠራጥሯል። ተቃዋሚዎችም መንግስት ምርጫውን አጭበርብሯል በማለት ሕዝቡን ልሰላማዊ ተቃውሞ እንዲነሳ ጥሪ አደረጉ። በዚህ ምክንያትም ሰላማዊ ሰልፈኞች የተገደሉ ሲሆን የተቃዋሚ መሪዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ደጋፊዎቻቸው የታሰሩ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ 11 የፓርላማ ተመራጮችና የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ይገኙበታል።

6. ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረትን ገዢው ኢሕአዴግ ተጭበረበሩ የተባሉትን ውጤቶች በሰላማዊ መንገድ በኢትዮጵያ ምርምጫ ቦርድ በኩል ለመፍታት ተስማሙ። ምርጫ ቦርዱ በ299 የምርጫ ውጤቶች ላይ ተቃውሞ የቀረበበት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በ31 ላይ ዳግም ምርጫ እንዲካሄድ የወሰነ ሲሆን፣ በፀጥታ ምክንያት ወደ ሌላ ወቅት ተሸጋግሮ የነበረው የሶማሌ ክልል 23 መቀመጫዎች ምርጫ በነሐሴ 2005 መጨረሻ አካባቢ አካሄደ።

7. የምርጫ ውጤቶች እንደሚያመላክቱት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በ2000 አግኝተውት ከነበረው 12 መቀመጫዎች በበለጠ 170 መቀመጫዎችን በብሔራዊ ፓርላምንቱ ማሸነፍ ቻሉ። በተጨማሪም ተቃዋሚዎች የዋና ከተማዋን የአዲስ አበባን ምክር ቤት በማሸነፋቸው ከተማዋን ለመቆጣጠር አስቻላቸው። ካሸነፉት 170 መቀመጫዎች 150 ያህል ተቃዋሚዎች ፓርላማ ገብተዋል። በግንቦት 2006 አካባቢ መንግስት ለከተማዋ ጊዜያዊ አስተዳዳር አቋቋመ። ቅንጅት ከተማዋን ያሸነፈ ቢሆንም፣ ተመራጩ ከንቲባ ከህዳር 2005 ጀምሮ በእስር ይገኛል።

8. ከግንቦት 2005 ምርጫ በኋላ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ በኢትዮጵያ የከፋ ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ ይህ ሁናቴም እስካሁን ምንም መሻሻል አላሳየም። የአሜሪካ የስቴት ዲፓርትመንት (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር) በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን በተመለከት ባቀረበው የ2005

ሪፖርት የኢትዮጵያ መንግስት አስጊ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ እንደፈጸመ ጠቁሟል። በተጨማሪም በነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችና ኤዲተሮች ላይ የፕሬስ ሕግ ጥሳቹሃል በሚል ሰበብ የሚደረገው እንግልትና እስራት ቀጥሏል። በደዘኖች የሚቆጠሩ ሀገሪቱን ጥለው የወጡ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ የህንን እንግልትና እስራት በመፍራት በውጭ ሀገር ተጠግተው የሚኖሩ ናቸው።

9. እንደ Human Rights Watch እና ሌሎች ዘገባዎች በሰኔ 2005 የኢትዮጵያ መንግስት ፀጥታ አስከባሪዎች 35 ሰላማዊ ሰልፈኞች የገደሉ ሲሆን በሕዳር 2005 ደግሞ 53 ሰላማዊ ሰዎችና 7 ፖሊሶች ተገድለዋል። የነዚህ ብጥብጦችና ግድያዎች መነሻ የግንቦት 2005 ምርጫ ወጤት በመቃወም የተቃዋሚዎች ደጋፊዎች ሰልፍ በወጡበት ወቅት ነበር። የተቃዋሚ ደጋፊዎች በመሆናቸው የተጠረጠሩ በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የታሰሩ ሲሆን ቆይቶ ግን ብዙዎች ተፈተዋል። አሁንም የተቃዋሚ መሪዎች፣ ደጋፊዎችና የቤተሰብ አባላት በፀጥታ ኃይሎች ማንገላታቸው አላቆመም።

10. 112 ያህል የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች፣ የሰብዓዊ መብቶች ተሚጋቾች፣ የህበረተሰብ መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የቅንጅት ሊቀ-መንበር ሃይሉ ሻውል፣ ተመራጩ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ብርሃኑ ነጋና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) መስራች ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ታስረው፣ የሀገር ክህደትና የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል። እነዚህ እርምጃዎች በሀገሪቱ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን በወንጀል ሰበብ ለማጨናገፍ ሆን ተብለው የተወሰዱ እርምጃዎች ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ እርምጃዎች የነፃው ፕሬስና የሲቪል ማህበረሰቡን ለማስፈራራትና ህልውናቸውን ለማጥፋት የተቃጡ ከመሆናቸውም በላይ፤ የኢትዮጵያ መንግስት ለዴሞክራሲና ለመልካም አስተዳደር ያለው ቁርጠኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው።

11. እንደ 2006 የስቴት ዲፓርትመንት የሀገራት የስብዓዊ መብቶች ሁናቴ ሪፖርት፡ “የሚከተሉት የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች በኢትዮጵያ እንደተፈፀሙ ሪፖርቱ ያትታል፡ ዜጎች በቅርቡ በተካሄደው ምርጫ መንግስታቸውን የመለውጥ መብታቸው መገደብ፣ ሕገ- ወጥ ግድያዎችና ድብደባዎች፣ እንግልት፣ እንዲሁም የታጋቾችና የተቃዋሚ ደጋፊዎች በፀጥታ ሃይሎች መንገላታት፣ ደረጃው የወረደ የእስርቤት ሁኔታውች፣ በዘፈቀደ እስራትና እገታ…”

12. እንደ የኢትዮጵያው ፓርላመንት፣ “ረብሻውን የሚመረምርና የሕዝብ ተውካዮች ምክርቤት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ሪፖርት የሚያደርግ” 11 አባላት ያሉት አጣሪ ኮሚሽን አቋቁሟል። ኮሚሽኑ የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች ተመጣጣኝ ያልሆነ ኃይል መጠቀማቸውን፣ በሕይውትና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን፣ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ መፈፀማቸውን እንዲያጣራ ሃላፊነት ተሰጥቶት ነበር። ኮሚሽኑ በሰኔ እና ሕዳር (June 8, 2005 እና November 1-10, 2005) በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች የተፈጠሩትን ረብሻዎች እንዲያጣራ ሃላፊነት ተጥሎበት ነበር።

13. እንደ አጣሪ ኮሚሽኑ ሪፖርት የኮሚሽኑ አባላት የተለያዩ ክልሎችን ጎብኝተዋል፤ የፖሊስ ሪፖርቶችን መርምረዋል፤ ከእስረኞችና ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር ተገናኝተዋል፤ 122 ጊዜ

የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስታውቂያዎችን ለሕዝብ አስተላልፈዋል፤ 16,990 ዶክመንቶችን መርምረዋል፤ እንዲሁም የ1,300 ሰዎች ቃል ተቀብለዋል።

14. እንደ አጣሪ ኮሚሽኑ ሪፖርት 763 ሰላማውያን ሰዎች እንደቆሰሉና 193 እንደተገደሉ ታውቋል። ኮሚሽኑ 71 ፖሊሶች እንድቆሰሉና 6 እንደተገደሉ ሪፖርት አድርጓል። $512,588 የሚገመት የንብረት ጉዳት ደርሷል። በተጨማሪም ከ30,000 በላይ ሰላማውያን ሰዎች እንደታሰሩ፣ የተወሰኑትም ስቃይ እንደደረሰባቸውና በቃሊቲ እስርቤት ታስረው የበሩም እንደተገደሉ ኮሚሽኑ አረጋግጧል።

15. እንደ አጣሪ ኮሚሽኑ ሪፖርት የፀጥታ ሃይሎች 1,500 ጥይቶችን በእስረኞች ላይ በመተኮስ፣ 17 ሰዎች ሲገደሉ 53 ቆስለዋል። ሰልፈኞቹ መሳሪያ እንዳልተጠቀሙና የባንክ ዘረፋም እንዳልፈፀሙ ኮሚሽኑ አትቷል። በሐምሌ (July 3, 2006) በኮሚሽኑ ዋና ዋና ግኝቶች ላይ የተካሄደው የውሳኔዎችና የድምፅ አሰጣጥ በቪድዮ-ቴፕ ተቀርጿል።

16. የአጣሪ ኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ ከደረሰ ከአጭር ጊዜ በኋላ፣ የኢትዮጵያ መንግስት የኮሚሽኑ አባላታ ውሳኔያቸውን እንዲወይሩ ጫና መፍጠር ጀመረ። የአጣሪ ኮሚሽኑ ሊቀመንበርና የቀድሞው የደቡብ ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት የነበሩት ኮሚሽኑን በአስቸኳይ በመሰብሰብ ውሳኔያቸውን እንዲቀይሩ በጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ከፍተኛ አማካሪ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር።

17. የአጣሪ ኮሚሽኑ ሪፖርቱን በሐምሌ (July 7, 2006) ለኢትዮጵያ ፓርላመንት ማቅረብ የነበረብት ቢሆንም፣ ፓርላመንቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ተበተነ። አብዛኛዎቹ የኮሚሽኑ አባላት፣ ሊቀመንበሩና ምክትሉ በእጃቸው የነበረውን ሪፖርት፣ ከማጣራቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ዶክመንቶች፣ እንዲሁም የውሳኔ ሂደቱን የሚያሳዩ የተለያዩ ቪድዮ ቴፖችን ይዘው ከሀገር ወጥተዋል።

18. በሕዳር (November 2006) የአጣሪ ኮሚሽኑ ሊቀመንበርና ሌላ አባል ለዩናይትድ ስቴትስ ኮንግረስ ሪፖርቱን እንዳቀረቡና ሰለዚህም ሪፖርት ማብራሪያ እንደሰጡ።

19. የአጣሪ ኮሚሽኑ አባላት በሕዳር (November 2006) ለኮንግረስ ማብራሪያ ባቀረቡበት ወቅት፣ ዓለምዙሪያ የተባለች ወጣት ሴት በእናቷ ወ/ሮ እቴነሽ ይማም ላይ ስለተፈፀመው ቃል ሰጥታለች። የዓለምዙሪያ አባት ግንቦት (May 2005) በተካሄደው ምርጫ ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ተመርጦ ነበር። ይህ ሆኖ እያለ የፀጥታ ኃይሎች አባቷን ለማሰር መጥተው በዚያውም ባለቤቷን እንዲለቁት ስትማፀን የነበረችውን ወ/ሮ እቴነሽን ተኩሰው ገድለዋታል።

20. የአጣሪ ኮሚሽኑ በዚያች አሰቃቂ ቀን የተፈፀመውን መርምሮ ወ/ሮ እቴነሽ ይማም መገደላቸውን ያለምንም ጥርጥር አረጋግጧል።

## ክፍል ፬. <u>በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ስለመርዳት</u>

**የስቴት ዲፓርትመንት ሴክረታሪ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር) ሊከናውኑ የሚገባቸው፦**

1. **የሰብዓዊ መብቶች ተንከባካቢ ድርጅቶችንና የነፃው ማህበረሰብ ተቋማትን በገንዝብ የሚረዱበትን መንገድ መሻትና በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች እንዲቆጣጠሩና ወቅታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ መርዳት፤**

2. **በኢትዮጵያ የፖለቲካና የህሊና እስረኞችን ደህንነት በተመለከት በንቃት የሚከታተሉ በኢትዮጵያ ውስጥና ውጭ ያሉትን ድርጅቶች የሕግ ድጋፍ መስጠት፤**

3. **በኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያዎች፣ የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የሚመለከታቸው የሕግ አውጭዎችና ዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብት ተንከባካቢ ድርጅቶች ተወካዮች መሃከል ውይይት በማድረግ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ገለልተኝነትና ነፃንት የሚጨምርበት አቅጣጫ መሻት፤**

4. **በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚገኙ ዓለማቀፋዊ ድርጅቶች በመላ ኢትዮጵያ የፍትሕ ሂደቶች የሚታዘቡበት መንገድ መፍጠርና በፍትህ ሂድት ውስጥ ሕገ-ወጥ የመንግስት ጣልቃ ገብነትን በማጣራትና በማጋለጥ ነፃ ፍርድ ቤቶች እንዲፈጠሩ መርዳት፤**

5. **እንደአስፈላጊነቱ የሞያ ስልጠናና ቴክኒካል ድጋፎችን በመስጠት በኢትዮጵያ የነፃው መገናኛ የሚጠናከርበትን መንገድ መገንባትና የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የፕሮግራም አቅርቦት ማስፋፋት፤**

6. **የአምባገነኑ የመንግስቱ ኃ/ማርያም ስርዓትና የወቅቱ የኢሕአዴግ መንግስት አባላት የሆኑና የሰብዓዊ መብቶችን የጣሱ በአሜሪካና በሌሎች ሃገራት የሚኖሩ መንግስቱ ሃይለማሪያምን ጨምሮ ለፍርድ የሚቀርቡበትን አቅጣጫ ማፈላለግ፤**

## ክፍል ፩. <u>በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ግንባታን ስለመደገፍ</u>

**ሀ. አካባቢያዊ፣ ክልላዊና አገር-አቀፍ የዲሞክየራሲ ግንባታን ለማበረታታት፦**

1. **ከመንግስት ባለስልጣናት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ከነፃው ማሕበረሰብ ተቁአማት ጋር በመመካከር አካባቢያዊ፣ ክልላዊና ሃገር-አቀፍ ምክርቤቶችንና መንግስታዊ አካላትን ማሰልጠንና ማጠናከር፤**

2. **በኢትዮጵያ መንግስት፣ ሰላማዊ የፖለቲካና የነፃው ማህበረሰብ ተቁአማት እንዲሁም ከአናሳ ሕብረተሰቦች ጋር ዕርቅ መፍጠርና ለድርድርና ለፖለቲካ ሂደቱ ተሳትፎ በር መክፈት፤**

3. **የፖለቲካ ድርጅቶችን ስለአደረጃጀትና ስለ ቅስቀሳ በመሳሰሉ ጉዳዮች ስልጠና በመስጠት ማጠናከር፤**

4. **የነፃው ማህበረሰብ ተቁአማት ሰለምርጫ ታዛቢነት ስለጠና መስጠት፤**

**ለ. <u>የዴሞክራሲ ግንባታ፦</u>**

1. ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ ለማበልፀግ የአሜሪካ መንግስት ለገዢው ፓርቲና ለተቃዋሚ ድርጅቶች ቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል።

<u>ገደቦች፦</u>

ሀ. ሰብዓዊ መብቶችን፣ ዴሞክራሲን፣ የፍርድ ቤቶችን ነፃነት፣ የመገናኛ ብዙኀን ነፃነት፣ የኢኮኖሚ እድገትንና የኢኮኖሚ ነፃነትን ለማጎልበት ያነጣጠረውን የአሜሪካን ቴክኒካል ድጋፍ የኢትዮጵያ መንግስት የሚያደናቅፍ ከሆነ፤ የአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጣቸውን መሠረታዊ ያልሆኑ እርዳታዎች ማቆም፤

ለ. <u>ማብራሪያ፦</u>
"መሠረታዊ ያልሆኑ እርዳታዎች" ሲባል - በሕግ መሠረት ከሰብዓዊ እርዳታ ውጭ የሆነ፣ በአደጋ ጊዜ ከሚሰጡ የምግብ እርዳታዎች ውጭ፣ እንዲሁም ለጤና እንክብካቤና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመግታት ከሚደረጉ እርዳታዎች ውጭ ማለት ነው።

## ክፍል ፤. <u>የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች፣ የዴሞክራሲና የኢኮኖሚ እድጋት እንዲሰፍን ስለሚሰጠው ድጋፍ ማረጋገጫ</u>

ሀ. <u>ለፀጥታ (ደህንነት) የሚሰጡ ድጋፎች ገደቦችና የጉዞ ገደቦች፦</u>

1. ለፀጥታ (ደህንነት) በሚመለከት የሚሰጡ ድጋፎች ገደብ

ሀ. ከዚህ በታች (አንቀፅ ፊደል ለ) ከተጠቀሰው ሁኔታ ውጭና በአንቀፅ ቁጥር 3 የተጠቀሰው ማረጋገጫ እስካልተሙአላ በስተቀር ለኢትዮጵያ የፅጥታ (ደህንነት) እርዳታ አለመስጠት፤

ለ. ከዚህ በላይ (አንቀፅ ፊደል ሀ) ላይ የተጠቀሰው የፅጥታ ገደብ ሰላም የማስጠበቅና ፀረ-ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የሚደረጉ እርዳታዎችን አይመለከትም። ሰላም የማስጠበቅና ፀረ-ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የሚደረጉ እርዳታዎች ከተጠቀሰው ዓላማ ውጭና የሰላማውያን ሰብዓዊ መብቶች የጣሱ የፅጥታ ኃይሎችና ቡድኖች ለማሰልጠን መዋል የለበትም።

2. <u>የጉዞ ገደብ፦</u>

ይህ ህግ ፀድቆ በስራ ላይ ከዋለበት ከ 60 ቀናት በሁአላና ከዚህ በታች አንቀፅ 3 ላይ የተጠቀሰው ማረጋገጫ እስካልተሙአላ ድረስ የአሜሪካ ፕሬዝደንት ከዚህ በታች የሠፈሩትን መስፈርቶች የሚመለከታቸው ግለሰቦችና ባለስልጣናት ወደ አሜሪካ የመግቢያ ቪዛ መከልከል

ሀ. ማንኛውም የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣን--

1. በኢትዮጵያውያን ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የኃይል እርምጃ እንዲወሰድ ትዕዛዝ በመስጠት የተሳተፉ፤

2. በሰብዓዊ መብቶች ረገጣ የሚወነጀሉ (የተወነጀሉ)፤

ለ. በ ሰኔ እና ኀዳር 2005 ዓ.ም. በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ተኩስ በመክፈት የተሳተፉ የኢትዮጵያ መንግስት የፅጥታ ኃይሎች፤

ሐ. በክፍል 3፣ በአንቀፅ 19 እና 20 እንደተጠቀሰው ወ/ሮ እቴነሽን በመግደል ተጥያቂ የሆኑት የፀጥታ ኃይሎች

መ. ከምርጫው በኋላ በተነሳው ብጥብጥ በቃሊትይ እስር ቤት ታስረው የነበሩ እስረኞችን የገደሉ የፀጥታ ኃይሎች

3. <u>ማረጋገጫ፦</u>

በዚህ አንቀፅ ላይ የተጠቀሰው ማረጋገጫ፣ የኢትዮጵያ መንግስት የሚከተሉትን መስፈርቶች ለማሟላት አስተማማኝና የሚለካ ጥረት ማድረጉን የአሜሪካው ፕሬዝደንት ለአሜሪካው የተወካዮች ምክርቤት የሚያቀርበው ማረጋገጫ ነው፤

ሀ. ሁሉም የኢትዮጵያ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ሲፈቱ፣ የሲቭልና የፖለቲካ መብቶቻቸው እንዲሁም ንብረታቸው ሲመለሱላቸው

ለ. ከኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት ውጭ ያለክስ የታሰሩ ወይም ያለፍርድቤት ትዕዛዝ የታገቱ ፈጣንና አግባብ ያለው ፍርድ ሲያገኙና ክሳቸው ውድቅ የተደረገ ካለምንም መዘግየት እንዲፈቱ፤

ሐ. የኢትዮጵያ የፍትሕ ስርዓት በነፃነት መስራት ሲጀምርና የኢትዮጵያን ሕገ-መንግስትና ዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብት መስፈርቶችን ማስጠብቅ ሲችል፤

መ. የሰላማዊ ሰልፈኞ ግድያ ማጣራት አስተማማኝ፣ ግልፅና ግድያውን የፈፀሙት ሲቀጡ፤

ሰ. የቤተሰብ አባላት፣ ጠበቃዎች እና ሌሎችም ጎብኝዎች በኢትዮጵያ እስርቤቶች ታግተው የሚገኙትን መጎብኘት ሲችሉ፤

ረ. የሕትመትና የብዙሃን መገናኛዎች በነፃነት ያለምንም ጣልቃ-ገብነትና ነፃነትን ከሚገድቡ ሕጎች ውጭ መሰራጨት ሲችሉና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሲሻሻሉ፤

ሠ. የግል ሬድዮና ቴለቪዥን ፈቃድ አሰጣጥ ክፍትና ግልፅ ሲሆን፤

ሸ. የኢትዮጵያ ዜጎች በኢንተርኔት አማካኝነት በነፃነት መገናኘት ሲችሉና መረጃ ያማግኘት ችሎታቸው ሲረጋገጥ፤

ቀ. በኢትዮጵያ የተወካዮች ምክርቤት መቀመጫ ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውስጥ ተወካዮች ሲኖራቸውና የምርጫ ቦርዱ በነፃነት የመወሰን ብቃት ሲኖረው፤

በ. በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች መርጋገጣቸውን የሚቆጣጠሩ የዓላምቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ተወካዮች ያለምንም ገደብ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ሲፈቀድላቸው፤

ተ. ሀገር በቀል የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ድርጅቶች ያለምንም ማስፈራራትና እንግልት በነፃነት መስራት ሲችሉ፤

ለ. <u>የፖለቲካና የህሊና እስረኞች አያያዝ</u>፦

1. የአሜሪካው ፕሬዝደንት፣ የስቴት ዲፓርትመንት ሴክርተሪና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለስልጣናት የፖለቲካና የህሊና እስረኞች በተለይም ያለምንም ክስ የታሰሩት በአፋጣኝ እንዲፈቱ ለኢትዮጵያ መንግስት ጥሪ ማቅረብ፤

2. ምንም አንኳን የሕገ-ወጥ እስርና ስቃይ እንዲሁም የተንገላቱና የቤተሰብ አባል የሞቱባቸው ቤተሰቦች የመካስ ሃላፊነት የኢትዮጵያ መንግስት ቢሆንም፤ የአሜሪካው ፕሬዝደንት ለተጎጂዎቹ እርዳታ እንዲደርስ ያደርጋል።

ሐ. የአሜሪካ ኮንግረስ አመለካከት፦ እንደ ኮንግረስ አመለካከት የአሜሪካ መንግስት የሚከተሉትን እንደሚያከናውን ይገነዘባል-

1. የኢትዮጵያ መንግስት ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር ውይይት እንዲጀምርና በኢትዮጵያ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ተሰታፊ እንዲሆኑና እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ሕጋዊነታቸው እኒዲጠበቅላቸው ማበረታታት፤ እንዲሁም

2. ከዚህ በላይ በአንቀጽ አንድ (1) ላይ የተምለከትውን ለማሳካት እንዲረዳ የሚያስፈልገውን ትብብር ማድረግ።

## ክፍል ፯. <u>የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገትን መደገፍ</u>

ሀ. የተፈጥሮ ሀብት ፖሊሲ አወቃቀር ድጋፍ፦ ፕሬዝዳንቱ በበዩናይትድ ስቴትስ የዓለማቀፍ ልማት ኤጀንሲ አስተዳዳሪ (USAID) በኩል ኢትዮጵያ የአባይና የአዋሽ ወንዞች ለዘላቂ እድገቷ እንድትጠቀምባቸው መርዳትና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመስኖና የሃይድሮ ኤለክትሪክ ግንባታዎችን እንድታከናውን በማድረግ ወደፊት ሊከስት የሚችል ድርቅን መከላከል።

ለ. የጤና እንክባቤ ስለመርዳት፦ ፕሬዝዳንቱ በዩናይትድ ስቴትስ የዓለማቀፍ ልማት ኤጀንሲ አስተዳዳሪ (USAID) በኩል በኢትዮጵያ ለሚገኙ ሆስፒታሎችና የጤና ጣቢያዎች፤ በተለይም በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል ለሚገኙ ሆስፒታሎችና የጤና ጣቢያዎች ቁሳዊ እርዳታ እንዲደርስ ያደርጋል።

## ክፍል ፰. *ሪፖርት*

***ይህ ህግ ከፀደቀ ከ*180 *ቀናት በኋላ፣ ፕሬዝዳንቱ የህጉን ተግባራዊነትና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መረጋጋትን የሚፈታተኑ የፅጥታ፣ የሰብዓዊ መብቶች፣የዴሞክራሲ ግንባታና የኢኮኖሚ ነፃነት ጉዳዮችን መፍታት የሚቻልባቸው ዝርዝር ዕቅድ ለኮንግረስ ሪፖርት እንዲያቀርብ።***

## ክፍል ፱. የተመደበ በጀት

***ሀ. በጠቅላላው- ይህንን ህግ ለማስፈፀም ለእያንዳንዱ በጀት አመት*** 2008-2009 ***ሊመደብ የሚችል*** $20,000,000 ***ይገኛል።***

***ለ. ከዚህ በላይ በአንቀፅ*** (*ሀ*) ***ላይ የተመደበው በጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ሕጋዊ ፈቃድ ካገኘ፣ ይህ በጀት በጥቅም ላይ እስኪውል ድረስ ሕጋዊ ፍቃዱ እንዲጠበቅ ይሁን።***